0085800007

Reçu CLT / CIH / ITH
Le 12 MARS 2012
N° 0197

# የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ (ኢባቅ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመመዝገብ የተዘጋጀ የኢንቬንተሪ ፎርማት (Format for National Register of the Intangible Cultural Heritage of Ethiopia)

መለያ ቁጥር - 0001

Register No - 0001

## 1. ዳራ (Background)

የመስቀል በዓል ኢንታንጀብል ቅርስ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላዊ ውርስ ነው፡፡

## 2. የኢንታንጀብል ቅርሱ መረጃ፡-

2.1 የቅርሱ ምድብ (Domain)፡- ማኅበራዊ ክንዋኔዎች፣ ሥነ-ሥርዓቶችና ፌስቲቫሎች (social practices, rituals and festive events) ነው፡፡

2.2 የቅርሱ ዓይነት መጠሪያ በብሔረሰቡ ቋንቋ፡- የመስቀል በዓል እንደየብሔረሰቡ አካባቢና ቋንቋ የተለያየ ሥያሜ አለው፡፡ ለምሳሌ በሃድያ፣ በወላይታ፣ በዳውሮና ጋሞ "መስቀላ"፣ በከምባታ "መሳላ"፣ በየም "ሂቦ"፣ በጉራጌ "መስቀር"፣ በኦሮሞ "ጉባ"፣ ወይም "መስቀላ" በካፊቾ እና ሻኬቾ "መሽቀሮ" በመባል ሲታወቅ በአማራና ትግሬዎች ዘንድ ደግሞ የመስቀል በዓል ተብሎ ይጠራል፡፡

2.3የቅርሱ ባለቤት፡- ብሔረሰብ፣ ቡድን ወይም ግለሰብ ስም፡-

የቅርሱ ባለቤት የአማራ፣ ትግሬ፤ ኦሮሞ፣ አዊ(አገው)፣ ጉራጌ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ኢሮብ፣ ሻኬቾ፣ ካፊቾ፣ ኮሬ፣ ሺናሻ፣ የዳውሮ ወዘተ ብሔረሰቦች ናቸው፡፡

2.4ስለ ቅርሱ ምንነት ማብራሪያ (Description)፡- መስቀል በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበር ብሔራዊ በዓል ነው፡፡ የመስቀል በዓል አጀማመር የክርስትና እምነት መሠረት የሆነው ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተቀበረበት ተቆፍሮ

መገኘትና (the finding of the True Holy Cross of Christ) በተለይም የመስቀሉ አንድ ክንፍ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በግሸን ዐምባ መቀመጥ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝት ቢኖረውም እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓሉን የሚያከብሩት እንደየብሔረሰቡ ባህል፣ አኗኗር፣ ወግ፣




የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመስቀልን ቅርጽ በመስራት ትርኢት ሲያሳዩ

ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ገጽታ ነው፡፡ የመስቀል በዓል ከሃይማኖታዊ ተልዕኮው ባሻገር የኢትዮጵያውያን ባህላዊ እሴት በመሆን ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ነው፡፡ በተለይ በአንዳንድ ብሔረሰቦች ዘንድ የመስቀል በዓል የበዓላት ሁሉ አውራ ሆኖ ከመታየቱ በተጨማሪ በዓሉ እንደ ዘመን መለወጫ የሚቆጠርና ለአዲሱ ዓመት የደስታ፣ የጤንነት፣የብልጽግና እንዲሆን ከመመኘት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የመስቀል በዓል በእያንዳንዱ የበዓሉ አከባበር ሂደት በእድሜ ደረጃና በፆታ የተለያዩ አካላትን ማለትም የወጣቶችን፣ የሴቶችንና የዐዋቂ ወንዶችን የቡድን ተሳትፎ የሚጠይቅ ደማቅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓል ነው፡፡

በተለይ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሚኖሩ ብሔረሰቦች ዘንድ የመስቀል በዓል ዝግጅት የሚጀመረው ቀደም ብሎ ሲሆን ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማሟላት ከወዲሁ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ ወንዶች የዕርድ በሬ ማደለብ ወይም ከገበያ ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ያጠራቅማሉ፡፡ በበዓሉ ሰሞን ለከብቶች ማሰማሪያ የሚውል የግጦሽ ቦታ ከልለው ያቆያሉ ወይም ሣር አጭደው ያከማቻሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ በበኩላቸው እንሰት ይፍቃሉ፣ አይብ፣ ቅቤና የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችን ያጠራቅማሉ፣ ባህላዊ መጠጦችን ይጠምቃሉ፡፡ ለበዓሉ የተለያዩ ምግቦችን ያዘጋጃሉ፡፡ ወጣት ወንዶች ለመስቀል በዓል የሚሆን የማገዶ እንጨት እና ለደመራና ችቦ የሚሆኑ እንጨቶችን ከጫካ ቆርጠው ያዘጋጃሉ፡፡ ልጃገረዶች በበዓሉ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችንና ምንጣፍ ያጸዳሉ፡፡ የወላጆቻቸውን ግቢ ያስውባሉ፡፡



**እንሰት ከመፋቁ በፊት የውጭው ሽፋን ከላዩ ላይ ሲነሳ- ዱራሜ**

የመስቀል በዓል መለያው ደመራው ነው፡፡ ደመራ ንግሥት እሌኒ ( Empress Helena) ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል በአይሁዶች ከተቀበረበት ለማውጣት በኢየሩሳሌም ቀራንዮ በሚባል አካባቢ በጐልጐታ ቁፋሮ ያስጀመረችበትን ቀን ለማሰብ የሚከበር ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ በሀገራችን የደመራ ሥነ ሥርዓት

በመጠኑም ቢሆን ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በትግራይ፣ በላስታና ላሊበላ፣ በአክሱም፣ በሰሜንና በደቡብ ወሎ፣ በዋግ ሕምራ፣ በከፊል ጐጃምና በአዊ ዞን ደመራው መስከረም 16 ቀን ቢደመርም ሥርዓተ ጸሎቱ የሚካሄደውና ደመራው የሚለኮሰው መስከረም 17 ቀን ንጋት ላይ ነው፡፡ በአንፃሩ አዲስ አበባን ጨምሮ በሸዋና በከፊል ጎጃም ደመራው የሚበራው በዋዜማው መስከረም 16 ቀን ምሽት ነው፡፡ የደመራው አደማመርና አበራር ሥነ-ሥርዓት ግን በሁሉም የኢትዮጲያ አካባቢዎች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው፡፡ የደመራ በዓል በብሔራዊ ደረጃ የሚከበረው በአዲስ አበባ በመስቀል አደባባይ ሲሆን እዚህ ደመራ የሚደመረውና ሥርዓት ጸሎት ተደርጎ የሚቀጣጠለው መስከረም 16 ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ማታ ነው፡፡ በዚሁ በዓል ላይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የአዲስ አበባና አካባቢዋ ነዋሪዎች በበዓሉ ሥነ-ሥርዓት ላይ ለመካፈል ወደ




**የመስቀል ደመራ በዓል በመስቀል አደባባይ-አዲስ አበባ**

መስቀል አደባባይ ይተማሉ፡፡ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶችና ቱሪስቶች በበዓሉ ላይ ይታደማሉ፡፡ ጥንግ ድርብ የለበሱ ሊቃውንት ያሬዳዊ መዝሙር ያቀርባሉ፤ ቅኔ ይቀኛሉ፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ለበዓሉ ድምቀት የሚሰጡ የተለያዩ ትርኢቶችን ያሳያሉ፤ ይዘምራሉ፤ ያሸበሽባሉ፡፡ የፌዴራል ፖሊስ ባንድ የሰልፍ

ትርኢትና በዘመናዊ መሣሪያ በመታገዝ ልዩ ልዩ ባዕመ ዝማሬን ያሰማል፡፡ ሠረገላ ይነዳል (ይጐተታል)፡፡ ፓትርያርኩ እና ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በዓሉን በተመለከተ አባታዊ ትምህርትና ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ደመራውን ባርከው ችቦ በእሳት በማያያዝ በሥነ ሥርዓቱ ላይ ከሚገኝ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ጋር በመሆን ደመራውን ይለኩሳሉ፡፡ ደመራው ወደ አመድነት እስኪለወጥ ይነዳል፡፡ በዚሁ ወቅት ሕዝቡ "እዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ" በማለት ይዘፍናል፡፡ ሴቶች እልል ይላሉ፡፡ ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ

ሕዝቡ አመዱንና ትርኳሹን እየተሻማ ወደቤቱ ይዞ ይሔዳል፡፡ አንዳንዶቹ በአመዱ ግንባራቸው ላይ የመስቀል ምልክት ያበጃሉ፡፡ አመዱ ለሰውም ሆነ ለከብቶች ፍቱን መድኃኒት ነው የሚል እምነት አለ፡፡ በደመራው ማግስት መስከረም 17 ቀን በሚከበረው ዋናው የመስቀል በዓል ምዕመኑ ቤተክርስቲያን አስቀድሶ ከተመለሰ በኋላ ሲበላና ሲጠጣ፣ ከጐረቤትና ዘመድ አዝማድ ሲገባበዝና ሲጠያየቅ በፍቅርና በደስታ



**ደመራው በመስቀል አደባባይ ሲቀጣጠል**

በዓሉን ሲያከብር ይውላል፡፡ የመስቀል በዓል በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች፣ በገጠርም በከተማም፣ በደብርም በገዳምም እንደ ኅብረተሰቡ ባህልና ልማድ በታላቅ አክብሮት በየዓመቱ ይከበራል፡፡ የኢትዮጵያውያን የመስቀል በዓል አከባበር ከተቀረው የዓለም ክፍል የተለየ (unique) በመሆኑና ወቅቱም ክረምቱ አልፎ የበጋ ወቅት

የሚጀመርበትና ጋራው ሸንተረሩ በአደይ አበባ የሚያሸበርቅበት በመሆኑ ቱሪስቶችን ወደ ኢትዮጵያ ከሚስቡ ክብረ በዓላት መካከል ዋንኛው ያደርገዋል፡፡

2.5 የቅርሱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ (Significance of the Intangible cultural Heritage) ሀገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦች ሃገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦች የየራሳቸው መለያ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችና ቅርሶች አሉዋቸው፡፡ እንደ መስቀል በዓል የመሳሰሉት ሃይማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት ደግሞ አብዛኞቹ ሕዝቦቿ በጋራ የሚያከብሯቸውና እርስ በርስ የሚያስተሳስሯቸው ናቸው፡፡ በዓለ መስቀል ሃይማኖታዊ በዓል መሆኑ ቢታወቅም የተለያዩ የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች በየራሳቸው ባህል፣ ትውፊትና እምነት አካሂድ ነው የሚያከብሩት፡፡ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል መንፈሳዊ ይዘቱ የገዘፈ ነው፡፡ በአንፃሩ በደቡብ ኢትዮጵያ መስቀል ከመንፈሳዊ ይዘቱ በበለጠ ባህላዊ ጐኑ ልቆ ይታያል፡፡ በዓሉ ካለው ሃይማኖታዊ ፋይዳ ባሻገር በርካታ ማኅበራዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ቅርሱ (በዓሉ) ካለው ፋይዳዎች አንፃር ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣

- ዓመቱን በሙሉ ተለያይተው የኖሩ የቤተሰብ አባላትና ዘመዳሞች የሚገናኙበትና የሚጠያየቁበት፣ ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን የሚፈቱበትና የሚረዳዱበት፣ ወጣቶች የሚተጫጩበትና ራሳቸውን ለጋብቻ የሚያዘጋጁበት፣ በጋብቻ የተሳሰሩ ቤተሰቦች የሚጠያየቁበት መሆኑ፣

- የተጣሉ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና በጥል የተለያዩ ባልና ሚስቶች ባጠቃላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተፈጠሩ አለመግባባቶችን በመፍታት እርቅ የሚወርድበትና ሰላም የሚሰፍንበት እንዲሁም በማኅበረሰቡ አባላት መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የጐላ ድርሻ የሚያበረክት መሆኑ፣

- እንደ ቤተሰብና አካባቢ በአዲሱ ዓመት የሚሠሩ ሥራዎች ተለይተው እንዴት መሠራት እንዳለባቸው የሚመከርበትና የሚታቀድበት እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች እዳ የሚሰረዝበት መሆኑ፣

- ወጣቶች በአባቶች የሚመረቁበት፣ ጐልማሶች ዕውቀቱን ከአባቶች የሚቀስሙበት፣ ኃላፊነት የሚረከቡበት፣ ለኢትዮጵያ ሀገራችን ሠላምና ብልጽግናን በመመኘት ጸሎት የሚደረግበት መሆኑ፣



ካህናቱ ሲያሸበሽቡ እና ያሬዳዊ መዝሙር ሲያቀርቡ

➢ ሕዝቡ የሚዘፍንበት፣ የሚጨፍርበት፣ የሚደሰትበት፣ ግጥም የሚገጥምበት ድምፁን የሚያሟሽበት፣ ወጣቱ የሚኮራበት፣ ባህሉን የሚያጠናበት፣ የሚለወጥበት ወቅት መሆኑ፣

➢ በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን ለበዓሉ ከምትሰጠው ሃይማኖታዊ ትርጉምና ሥርዓት በመነሳት በብዙ የሃገራችን ብሔሮችና ብሔረሰቦች ዘንድ ጥልቅ የሆነ የመተሳሰብ፣ የፍቅር፣ የወዳጅነት መንፈስ የሚጐለብትበት ወቅት ነው፡፡

# 3 የቅርሱ መለያ ባሕርያት

## 3.1 የቅርሱ ቁሳዊ መገለጫ(associated tangible aspects)፡-

በበዓሉ አከባበር በተለይ በደመራ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የየአድባራቱ ካህናት ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው፣ መዘምራኑ በጥንግ ድርብ አጊጠው፤ ከበሮ፣ ማቋሚያና ጽናጽል ይይዛሉ፡፡ በመስከረም 16 ቀን ታላቅ የሆነ የመስቀል

ደመራ በዓል ይደረጋል፡፡ በደመራው በዓል ረጃጅም እንጨት ከየአካባቢው እየመጣ አንድ ላይ ተሰብስቦ ይደመራል፡፡ የጸሎት ሥነ-ሥርዓቱ ካበቃ በኋላ ፓትሪያርኩ ደመራውን ባርከው ችቦውን አብርተው ደመራው ይለኮሳል፡፡



የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲዘምሩ

በደቡብ ኢትዮጵያ ከበዓሉ አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሳዊ መገለጫዎች ደግሞ ከሸክላ የተሰሩ አይብና ክትፎ የሚቀርብባቸው ጣባዎች፣ ጥዋ፣ ገበቴ፣ መክተፊያ፣ ከቀንድ የሚሰራ በህላዊ ጭልፋ፣ ክትፎ በእጅ ላይ ተደርጎ የሚበላበት ቅጠል (ጥለስ)፣ ምንጣፎች እና በሬ ማረጃ ካራ የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

**3.2የቅርሱ አካላዊ መገለጫ፡-** የመስቀል በዓል በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ ልዩ ግምት ተሰጥቶት በከፍተኛ ዝግጅትና ድምቀት በየዓመቱ የሚከበር ክብረ በዓል ነው፡፡ በደመራው ሥነ-ሥርዓት ላይ በሽብሸባ ታጅቦ ያሬዳዊ መዝሙር በካህናቱ ይቀርባል፡፡ ከበሮ ይመታል (ይጎሰማል)፡፡ የሰንበት ት/ቤቶች ወጣት መዘምራን ይዘምራሉ፡፡ የተለያዩ ትርዒቶችንም ያቀርባሉ፡፡ የበዓሉ ታዳሚ ምእመናንም ዕልልታውንና ጭብጨባውን ያቀልጡታል፡፡ ፍጹም ደስታና

ዕልልታ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ደመራው ይቃጠላል፡፡ በዚህም መሠረት ከዋዜማው ጀምሮ ሲዘፈን፣ ሲጨፈር ይታደራል፡፡ በዓልን ከዋዜማ ጀምሮ ማክበር በኢትዮጵያ የተለመደ ነው፡፡ ከዋዜማው ቀጥሎ በማግስቱ መስከረም 17 ቀን ዋናው የመስቀል በዓል ይከበራል፡፡

## 4. ኢንቬንተሪ ከተደረገው ቅርስ ጋር በተያያዘ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት

### 4.1 የቅርሱ ተግባሪዎች(አከናዋኞች)፡-

በሀገር አቀፍ ደረጃ ኢንቬንተሪ ከተደረገው የመስቀል በዓል ጋር በተያያዘ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦችና የቅርሱ ተግባሪዎች ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ ካህናት፣ የጽዋ ማኅበር አባላት እና የሰንበት ት/ቤቶች መዘምራን ናቸው፡፡

### 4.2 ሌሎች ተሳታፊዎች ባለቤቶች/ ጠባቂዎች፡-

በተቋም ደረጃ የቅርሱ (የበዓሉ) ባለቤት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስትሆን ቅርሱን በመንግሥት ደረጃ ለመጠበቅ የተቋቋመው መ/ቤት ደግሞ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥል ጣንና ክልላዊ መንግሥታት ሥር የሚገኙ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ናቸው፡፡

### 4.3 ቅርሱን ለማየት ወይም ለመድረስ ያሉ ሥርዓቶችና ደንቦች (Access rules or procedures)፡-

አብዛኛው የመስቀል በዓል ሥነ-ሥርዓቶች ለታዳሚዎች ለቱሪስቶችም ሆነ ለተመራማሪዎች ክፍት ሲሆኑ ከበዓሉ ጋር በተያያዘ ለማየት ወይም ለመድረስ ክልከላ የሚደረግበት አንድ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ይህ በግሸን ደብረ ከርቤ የሚገኘው ግማደ መስቀል ሲሆን ለዚህ ውድ ቅርስ ደህንነት ሲባል ቅርሱን ለማየት ወይም ለመድረስ ገደቦች አሉ፡፡

## 5 የቅርሱ ቀጣይነትና ደህንነት፡-

### 5.1ቅርሱ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ(current status)፡-

የመስቀል በዓል በአሁኑ ወቅት በታላቅ ድምቀት ከሚከበሩ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ በዓላት መካከል አንዱና ዋንኛው ነው፡፡ የመስቀል በዓል በሀገራችን በከተማም ሆነ በገጠር እጅግ ባማረና በደመቀ ሁኔታ ከሚከበርባቸው መንገዶች አንዱ በታላላቅ አድባራትና ገዳማት ቅጥር ግቢ እንዲሁም ለሕዝቡ ማዕከል በሆኑ አደባባዮችና በየመኖሪያ ቦታዎች የሚከናወነው የደመራ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ በዚህም ወቅት ካህናቱ የዕለቱን ጸሎት ካደረሱና አስፈላጊውን ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት ሁሉ በሚገባ ከተከናወነና ደመራው ከተባረከ በኋላ በእሳት ይለኮሳል፡፡ ሕዝቡም ‹‹ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ›› በማለት ደመራውን እየዞረ ለበዓሉ ያለውን ክብር ይገልጻል፡፡ መጪው ዘመን የሰላምና የጤና እንዲሆንለት በመመኘት በየቋንቋውና በየባህሉ ለፈጣሪው ምስጋናውን የሚያቀርብበትና ወጣቶች የሚመረቁበት ነው፡፡ ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ በተጨማሪ በሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል ከሃይማኖታዊና ከባህላዊ አከባበሩ ባሻገር የቱሪስት መስህብ በመሆን ይታወቃል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል በበዓሉ አከባበር ሥነ-ሥርዓት፣ በሕዝቡ ብዛትና በትርዒቱ ማማር ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን በከፍተኛ ደረጃ እየሳበ ይገኛል፡፡

### 5.2ቅርሱን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገዶች፡-

ስለ በዓሉ አከባበር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን እውቀት ማስተላለፊያ ከሆኑ መንገዶች መካከል አንዱ በዓሉ በተለይ የደመራው ሥነ-ሥርዓት የሚከበረው በአደባባይ በመሆኑ ወጣቶችም ሆኑ ሌሎች በበዓሉ ሥነ-ሥርዓት ላይ በመገኘት ምልከታ እና ተሳትፎ በማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም የበዓሉ አከባበር ታሪካዊ አመጣጥና ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በተመለከተ ከሃይማኖት አባቶችም ሆነ የሀገር ሽማግሌዎች የሚሰጠውን የቃል ትምህርት በመከታተልና በማዳመጥ ነው፡፡ ሌላው በአንዳንድ ክልሎች የመስቀልን በዓል አስመልክቶ የሚዘጋጁ ፌስቲቫሎች ላይ በመታደም በበዓሉ ወቅት የሚዘጋጁ ምግቦች የአሠራር ሂደት፣ በበዓሉ አከባበር ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶች፣ ባህላዊ ጭፈራዎችን በመመልከትና እንደ አስፈላጊነቱ

ተሳትፎም በማድረግ ጭምር ነው፡፡ ቅርሱ በክልል እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ምዝገባ (ኢንቬንተሪ) ሲካሄድ የተቀሰሙ ልምዶችን በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተትና እውቀቱ ለቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍበት ሥርዓት እየተበጀ ይገኛል፡፡ የበዓሉን አከባበር በተለያዩ ብሔረሰቦች ዘንድ የሚያሳዩ ምስሎች በቪዲዮ በመቅረጽና መረጃውን በብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችና በራዲዮኖች በማስተላለፍና ስለ በዓሉ በየጊዜው የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በተለያዩ ሚዲያዎች ይፋ በማድረግ ቅርሱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 5.3 ቅርሱን ለመተግበር ያሉ ሥጋቶች፡-

### 5.3.1 አካላዊ ወይም ቁሳዊ ሥጋት (Physical threats)፡-

ለመስቀል በዓል ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች ትግበራ እንቅፋት የሆኑ አካላዊ ሥጋቶች ብዙም አይታዩም፡፡

### 5.3.2 ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥጋቶች (Socio economic threats)፡-

በኢትዮጵያ ብቻ በሚከበረውና እንዲሁም በትርዒቱ ማማርና ደማቅነት ልዩ በሆነው የደመራ በዓል አከባበርን ለመመልከት ከመላው ዓለም የሚመጡ ቱሪስቶችና ጋዜጠኞች ከሚመለከተው አካል ፍቃድ ውጭ ስለ በዓሉ አከባበር በሲዲ እና በፖስት ካርድ አሳትሞ መሸጥ እና ባጠቃላይ በዓሉ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ፈሩን እንዲለቅ (over commercialize) ማድረግ በዓሉን እያጋጠሙ ካሉ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሥጋቶች መካከል በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ሌላው ሥጋት የመስቀል በዓልን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ቀኖና ከሚፈቅደው ውጭ ወይም የሚጻረር የሌሎችን ሃይማኖታዊ እምነት በበዓሉ ላይ ማንጸባረቅ፣ ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን ማንሳት እና የወሲብ ቱሪዝምን ማስፋፋት የመሳሰሉ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥጋቶች ሊጋረጡበት ይችላሉ፡፡

## 5.4 ለቅርሱ ቀጣይነት እየተደረጉ ያሉ እንክብካቤዎች፡-

- የመስቀል በዓል ባሕላዊ ይዘቱን ጠብቆ የኢትዮጵያውያን የማንነት መገለጫ ሆኖ እንዲቀጥል የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም

መካከል ለቅርሱ ጥበቃ የሚያግዙ ሕጋዊ ማዕቀፎችን በማውጣት፣ ቅርሱን በክልል እና በሀገር አቀፍ ደረጃ መመዝገብ፣ የበዓሉ ሥነ-ሥርዓት በሚካሄድበት ወቅት በቪዲዮ ዶክመንት በማድረግ እና በተለያዩ ሚዲያዎች የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ጭምር በመጠቀም ማስተዋወቅ፣ በዓሉን በተመለከተ በኢንቬንተሪም ሆነ በጥናትና ምርምር የተገኙ እውቀቶችንና ልምዶችን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተት፣ የሀገር ሽማግሌዎችና አዋቂዎች ስለ ቅርሱ ምንነትና ጠቀሜታ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለወጣቶች ማስተዋወቅ የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

## 6 የመረጃ አሰባሰብና ጥንቅር፡-

6.1 በኢንቬንተሪው ወቅት የህብረተሰቡ፣ የቡድኖችና ግለሰቦች ተሳትፎ መገለጫዎች፡- በመስክ ሥራ ወቅት ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን መረጃ በመስጠት ከፍተኛ ትብብር አድርገዋል፡፡

6.2 ኢንቬንቶሪ የተደረገውን ቅርስ መረጃ ለመጠቀም ያሉ ገደቦች፡- ያለፍቃድ ለንግድም ሆነ ለሌላ ዓላማ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

6.3 ምዝገባው የተካሄደበት ወቅት፡- ነሐሴ 14/2003 (August 20,2011) ሲሆን የምዝገባ መለያ ቁጥሩ 0001 ነው፡፡

6.4 ቅርሱን በሀገር አቀፍ ደረጃ በቅርስነት የመዘገበው አካል፡- ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን (Authority for Research and conservation of cultural Heritage) ነው፡፡

የቅርስ ኢንቬንተሪ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር